አሐዱ፡ባንክ

Ahadu Bank

የአክሲዮን ሽያጭ መረጃ

ለነባር እና አዲስ ባለአክሲዮኖች

## 1. አጠቃላይ መረጃዎች

1.1. አክሲዮን የሚገዙ ነባርና አዲስ ባለአክሲዮኖች ኢትዮጵያዊነታቸውን ወይም በትውልድ ኢትዮጵያዊ መሆናቸውን የሚገልፅ የታደሰ መታወቂያ ካርድ (ሕጋዊ ሰውነት ላላቸው ድርጅቶች የመመሥረቻ ጽሁፍ) ማቅረብና ለዚሁ ዓላማ የተዘጋጀውን የአክሲዮን መግዥያ ቅፅ መሙላት የሚኖርባቸው ሲሆን በውክልና ለሚፈጸሙ የአክሲዮን ግዢዎች አክሲዮን መግዛት የሚያስችል የውክልና ሥልጣን ማስረጃ በተጨማሪነት መቅረብ ይኖርበታል ፡፡

1.2. የአንድ አክሲዮን ዋጋ(Par Value) ብር 500 ሆኖ አንድ ባለአክሲዮን መግዛት የሚችለው ዝቅተኛ የአክሲዮን መጠን ለኢትዮጵያዊ ባለአክሲዮኖች 40 (አርባ) አክሲዮኖችን ወይም 20,000.00 ብር ሲሆን በትውልድ ኢትዮጵያዊ ሆነው የውጪ ሀገር ዜጋ ለሆኑ ባለአክሲዮኖች ዝቅተኛ መግዛት የሚቻለው የአክሲዮን መጠን 100(አንድ መቶ) አክሲዮኖችን ወይም 50,000.00 ብር ነው ፡፡

1.3. አንድ ባለአክሲዮን ከፍተኛ መግዛት የሚችለው የአክሲዮን መጠን 99,999,500 ብር ድረስ ብቻ ነው፡፡

1.4. የአከፋፈሉ ሁኔታ በተመለከተ ባለአክሲዮኖች ለመግዛት የፈረሙትን አክሲዮኖች ዋጋ መሉ በሙሉ በአንድ ጊዜ ወይም በአንድ ጊዜ ክፍያ መፈጸም የማይችሉ ባለአክሲዮኖች የተፈረሙትን አክሲዮኖች ዋጋ 25% እንዲሁም 5% የአገልግሎት ክፍያ በቅድሚያ በመክፈል ቀሪውን በሦስት ዓመት ጊዜ ውስጥ በኢትዮጵያ አቆጣጠር እስከ ታኅሣሥ 30 2018 ዓ.ም ከፍለው ማጠናቀቅ ይኖርባቸዋል፡፡

1.5. የአገልግሎት ክፍያ (Service charge) በተመለከተ የሚሰላው በተፈረሙ አክሲዮኖች መጠን ሆኖ ክፍያውም ሙሉ በሙሉ ከመጀመሪያው ክፍያ ጋር ተጠቃሎ የሚፈጸም ሲሆን ነባር ባለአክሲዮኖች ከአገልግሎት ክፍያ ነጻ ናቸው፡፡

## 2. ዜግነታቸው ኢትዮጵያዊ የሆኑ ባለአክሲዮኖች

2.1. አክሲዮኖች የሚሸጡት በአሐዱ ባንክ ቅርንጫፎች ነው፡፡

2.2. ባለአክሲዮኖች የአክሲዮን ክፍያዎቻቸውን ከሒሳባቸው ወይም በጥሬ ገንዘብ መፈጸም የሚችሉ ሲሆን ለፈጸሙት ክፍያ ተገቢውን የባንክ አድቫይስ(ደረሠኝ) እና በባንኩ የተፈረመና ማህተም የተደረገበት የአክሲዮን መግዥያ ቅፅ 1 ኮፒ ክፍያውን ከፈጸሙበት ቅርንጫፍ መቀበል ይኖርባቸዋል፡፡

## 3. በትውልድ ኢትዮጵያዊ የውጪ ሀገር ዜጋ የሆኑ ባለአክሲዮኖች

3.1. ክፍያዎች በባንኩ ተቀባይነት ባላቸው የውጪ ሀገር ምንዛሪ (currency)በዋነኝነት በ USD, EURO እና GBP የሚከፈል ይሆናል፡፡

3.2. አክሲዮን ለመሙላት የሚሞሉ ፎርሞችንና የመክፈያ አማራጮችን በባንኩ ዌብ ሳይት ahadubank.com/sharesale ላይ በመግባት ማግኘት ይችላሉ፡፡

3.3. ትውልደ ኢትዮጵያዊ የሆኑ ባለአክሲዮኖች የአክሲዮን ክፍያዎችን ባንኩ ባስቀመጠላቸው የመክፈያ አማራጮች ብቻ መክፈል የሚኖርባቸው ሲሆን ትውልደ ኢትዮጵያዊ መሆናቸውን የሚገልፅ የአክሲዮን መግዣ ቅፅ፣ ክፍያ የፈጸሙበትንና ሌሎች ማስረጃዎችን ክፍያ በፈጸሙበት ቀን አሟልተው በኢሜል አድራሻ Sharesale.f@ahadubank.com መላክ ይኖርባቸዋል፡፡

Ahadu Bank, HQ
Share Sales Department
Addis Ababa, Ethiopia
Tel: + 251 11 526 10 23
+251 115 26 07 87
ahadubank.com